የሰ/መ/ቁጥር 211427

ግንቦት 26 ቀን 2014ዓ/ም

ዳኞች፡- እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- አቶ ዓለሙ ጋዲሞ

ተጠሪዎች፡-1) ወ/ሮ ትርንጎ ዳንሼ

2) ወ/ሮ ሽቶ ዳንሶ የቀረበ የለም

3) ወ/ሮ ብርቱካን ደንገሶ

4) አቶ ደስታ ደንግሶ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0030 ታሕሣስ 13 ቀን 2014ዓ/ም በዋለው ችሎት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት አይደለም ሲል አቤቱታውን መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈፀመበት ነው በሚል እንዲታረምለት አመልካች በመጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በሶዳማ ዞን ዳራ ኦትልቾ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳ ፍርድ ቤቱ በነበረው ክርክር አመልካች ከሣሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ጥቅምት 16ቀን 2011ዓ/ም በተፃፈ ክሱ ከተጠሪዎች ጋር በገባው የመሬት መጠቀም ውል ሣይፈርስ ተጠሪዎች ባቀረቡት የሀከት ክስ መሬቱን እንዲለቅ በመሬቱ ላይ ላፈራው ንብረት ግምትን በሚመለከት በዳኝነት እንዲጠይቅ

መወሰኑ መነሻ በማድረግ በመሬቱ ላይ አፍርቻቸዋለሁ የሚላቸውን 23 ዓይነት አትክልችና ልዩ ልዩ ንብረቶች በመዘርዘር በባለሙያ ተገምተው እንዲከፈለው ጠይቋል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው የተዘረዘሩ ንብቶች አመልካችን የሚመለከቱ አለመሆናቸውን፣ አመልካች ማስረጃ እንዲሆነው ያቀረበው ውልም ከእነሱ ጋር የተፈፀመ አለመሆኑን በመቃወሚያነት አቅርበው ውድቅ ሲደረግ በፍሬ ነገር ረገድ ደግሞ አንደኛ ከተጠሪ ጋር የገቡት ውል አለመኖሩን ከገለፁ በኋላ ሁሉም ተጠሪዎች በጋራ ሆነው ለክሱ ምክንያት የሆኑትን አትክልቶች የ1ኛ ተጠሪ ባለቤት ከ2ኛ እስከ 4ኛ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ በሕይወት ሳሉ የተከሏቸው በመሆናቸው አመልካችን የማይመለከቱት ናቸው ሲሉ ተከራካረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤት በአንደኛ ተጠሪ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ ካደረገ በኋላ የግራ ቀኙን ምስክሮች የሰጡትን ምስክርነት መርምሮ ቀደም ሲል በነበረው ክርክር አመልካች በመሬቱ ላይ ላፈራው ንብረት ግምት እንዲጠይቅ የተፈቀደለት መሆኑን፣ በዚሁ መሰረት የግብርና ባለሙያ አመልካች በመሬቱ ላይ ያፈራው ንብረት በአንድ ዓመት ምን ያህል እንደሚያወጣ ገምቶ እንዲልክ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት በዓመት 26,066.00 ብር እንደሚያወጣ መልስ ተሰጥቶታል፡፡ ፍርድ ቤቱም ይህን የባለሙያ ግምት በ10ዓመት በማባዛት ውጤቱን ለሁለት በማካፈል 130,330.00 ብር ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር የተሰኙት ተጠሪዎች የይግባኝ አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግብርና ባለሙያ ገምቶ የላከውን ግምት በ10 አባዝቶ ለሁለት አካፍሎ የተገኘውን ውጤት ተጠሪዎች እንዲከፍሉ የመወሰኑን ተገቢነት በጭብጥነት ይዞ ከመረመረ በኋላ ውሉ የፈረሰው ሕገወጥ ነው በሚል ስለሆነ የጊዜ ገደብ የሌለበትን ውል ወደፊት በ10 ዓመት የሚገኘውን ጥቅም ታሣቢ በማድረግ በ10 ማባዛቱ ተገቢነት የሌለው ነው ሲል ተጠሪዎች 26,066.00 ብር ብቻ ለአመልካች እንዲከፍሉት ሲል አሻሽሎ ወስኗል፡፡

አመልካች በበኩሉ የይግባኝ አቤቱታውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የስር ፍርድ ቤቱን ውሣኔ የማሻሻሉን ተገቢነት በጭብጥነት ይዞ ከመረመረ በኋላ ውሣኔውን አፅንቶታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ሲል አቤቱታውን በመሰረዙ አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

አመልካች ሚያዚያ 12ቀን 2013ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታው የስር ፍርድ ቤቱ የንብረቱን ግምት በባለሙያ እንዲገመት ካደረገ በኋላ በግምቱ ላይ ግራ ቀኙ አስተያዬት እንዲሰጡበት ሣይደረግ፣ ግምቱ መገመት ያለበት የአንድ ዓመት ሣሆን ተቆርጦ ቢሸጥ የሚያወጣውን ዋጋ በመሆኑ እንደገና ተገምቶ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት ሲገባ፣ በቀረበው ክስ በባለሙያ ተገምቶ እንዲከፈለው ጠየቀ እንጅ ለሁለት ተካፍሎ የአንድ ዓመት ግምት እንዲሰጠው ባልጠየቀበት ከላይ የተገለፀውን ውሣኔ መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተው ተብሎ እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ቀደም ሲል በግራ ቀኙ በነበረው ክርክር አመልካች መሬቱን ለቆ እንዲወጣ ሲወሰንበት በመሬቱ ላይ ያለማውን የንብረት ግምት ይከፈለው ዘንድ ክስ ማቅረብ እንደሚችል  ተወስኖለታል በሚል በጠቅላላው የንብረት ግምቱ በአስር ዓመት ተባዝቶ እንዲከፈል የተሰጠውን ውሣኔ ዳኝነት ያልተጠየቀበት ነው ተብሎ የበላይ ፍርድ ቤቶች የአንድ ዓመት ግምት ብቻ እንዲከፈል የወረዳው ፍርድ ቤትን

ውሳኔ በማሻሻል የመወሰናቸው አግባብነት እንዲጣራ ተብሎ ጉዳዩ ቀርቦልናል፡፡

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ተጠሪዎች በበኩላቸው መጋቢት 1ቀን 2014ዓ/ም በተፃፈ የጋራ መልሳቸው ቀደም ሲል በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል የነበረው ክርክር ከአባታቸው በውርስ ያገኙትን መሬት አመልካቹ ስለያዘባቸው እንዲለቅላቸው ክስ አቅርበውበት አመልካች መሬቱን ገዝቻለሁ የሚል ክርክር አቅርቦ ውሉ ሕገወጥ ነው ተብሎ በመሬቱ ለተከላቸው ተክሎች ግምት እንዲጠይቅ በተጠበቀለት መብት መሰረት ክስ ማቅረቡን፣ ንብረቶችም በባለሙያና በሽማግሌዎች ተቆጥረው በግራቀኛቸው ስምምነት ተደርጎ ተፈራርመውበት ባሙያው ግምቱን ሰርቶ መላኩን፣ በዚህ በባለሙያ ግምት መሰረት የወረዳ ፍርድ ቤቱ መወሰን ሲገባው በአስር ዓመት አባዝቶ እንዲከፈል መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ በከፍተኛው ፍርድ ቤት መሻሻሉ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሌለ የስር ፍርድ ቤቱ ውሣኔ እንዲፀናላቸው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ የሰበር አቤቱታውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርቦ የግራ ቀኙ ክርክር ተጠናቋል፡፡

ከፍ ሲል በአጭሩ የተመለከትነው የጉዳዩን አመጣጥኛ የግራ ቀኙን ክርክር ሲሆን አጣሪ ችሎቱ ከያዘው ማስቀረቢያ ነጥብ አኳያ የተፈፀመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የግራ ቀኙን ክርክር ቅሬታ ከቀረበበት የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ ውሣኔና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተመርምሯል፡፡

እንደተመረመረው ቀደም ሲል በነበራቸው ክርክር አመልካች መሬቱን እንዲለቅ የተወሰነው ውሉ ሕገወጥ ተብሎ መሆኑ፣ አመልካች ያቀረበው ክስ ቀደም ሲል በተሰጠው ውሳኔ የተጠበቀለትን መብት መነሻ በማድረግ በክሱ ላይ የተዘረዘሩት ንብረቶች ግምት በባለሙያ ተገምቶ እንዲከፈለው እንዲወስንለት መሆኑ፣ ባለሙያው በቦታው ተገኝቶ የገመተው 26,066.00 ብር መሆኑ ግራ ቀኙን ያላከራከረ ነበር፡፡

የስር ወረዳ ፍርድ ቤቱ በባለሙያ ተገምቶ የቀረበለትን ግምት በ10ዓመት አባዝቶ እንደገና ለሁለት አካፍሎ የተገኘውን ድርሻ ተጠሪዎች ለአመልካች እንዲከፍሉ ከመወሰኑ ውጪ ለምን እንደሆነ ምክንያቱን በግልፅ አላሰፈረም፡፡ ይግባኝ ሰሚ የሆነው ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በማሻሻል የአንድ ዓመት ብቻ እንዲከፍል ሲወስን አመልካች የአስር ዓመት ግምት እንዲከፈለው አልጠየቀም በሚል ምክንያት ነው፡፡ በአመልካች በኩል የንብረቱ ግምት በባለሙያ ተገምቶ እንዲከፈለው ከመጠየቁ ውጪ የአስር ዓመት እንዲከፈለው መጠየቁን አይከራከርም፡፡

በመሰረቱ ፍርድ ቤቶች የቀረበላቸውን ሙግት አጣርተው ውሣኔ ወይም ፍርድ ሲሰጡ በተከራካሪ ወገኖች በተጠየቁት ዳኝነት አይነትና ልክ ሊሆን እንደሚገባ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር182(2) የሚደነግግ ሲሆን ባልተጠየቀ ዳኝነት ፍርድ ወይም ውሣኔ መስጠት የማይቻልና ተገቢነት የሌለው መሆኑን ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 31547 መጋቢት 7ቀን 2000ዓ/ም እና በመዝገብ ቁጥር 33945 ጥቅምት 20ቀን 2001ዓ/ም የሰጠው

የሕግ ትርጉም ያስገነዝባል፡፡ ሲጠቃለል ከይግባኝ ሰሚ ጀምሮ በየደረጃው የሚገኙት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

*ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

ውሣኔ

1) የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0030 ታሕሣስ 13 ቀን 2014ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348(1) ፀንቷል፡፡

2) ይህ የሰበር ክርክር ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የዬራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሠ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም